Amhariska

Socialstyrelsen

# የሴት ብልት
# ጉንደላ

tryckeri: Ale Tryckteam, Bohus, maj 2003
grafisk form: Typoform AB
artikelnummer: 2003-114-12
ISBN: 91-7201-727-9

ይህ ጽሑፍ የሴት ብልት ጉንደላ ወይም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ
የሴት ግርዛት የሚባለውን ድርጊት ይመለከታል።

- ማንኛውም ዓይነት የሴት ብልት ጉንደላ በስዊድን ሕግ የተከለከለ ነው።

- የሴት ብልት ጉንደላ በሃይማኖት ጽሑፎች የታዘዘ አይደለም።

- የሴት ብልት ጉንደላ የሴቶችንና የልጆችን ጤንነት የሚጎዳ ነው።

ይህም በሚከተሉት ገጾች ዘርዘር ተደርጎ ይገለጣል። «የሴት ብልት
ጉንደላ» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ጽሑፍ በእንግሊዝኛ፣ በሶማልኛ፣
በትግርኛና በአማርኛ ተተርጉሞ ይገኛል።

ጽሑፉ የወጣው ከ RFSU ጋር ካለው የቅርብ የሥራ ትብብር ነው፣
የተመሠረተውም RFSU ቀደም ብሎ ባሳተመው አንድ ጽሑፍ ላይ ነው።

# መግቢያ

## አንቀጽ 1

ሰው ሁሉ የተወለደው ነፃ ሆኖ ነው። ሁሉም እኩል ባለዋጋና ባለመብት ነው። ሁሉም አእምሮና ኅሊና ስለ አለው እርስ በርሱ ባለው ግንኙነት አንድ ቤተሰብ እንደ ሆነ ዓይነት መተያየት ይገባዋል።

## አንቀጽ 2

ሰው ሁሉ በዚህ መግለጫ ውስጥ የተመለከቱት ነፃነቶችና መብቶች ይኖሩታል። የሌላ ዘር በሆነ ወይም ሌላ የቆዳ ቀለም ባለው ሰው ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት መደረግ የለበትም። ለልጃገረዶችና ለወንዶች ልጆች ወይም ለሴቶችና ለወንዶች [...] የተለያዩ መብቶች እንዲኖሩ መደረግ የለበትም።

## አንቀጽ 3

ሰው ሁሉ የመኖር መብት አለው። ሁሉም ስለ ገዛ ሕይወቱ ራሱ ለመወሰን የሚችልበት ነፃነት ይኖረዋል። ሁሉም ካለ ስጋትና ጭንቀት ለመኖር የሚችል መሆን አለበት።

## አንቀጽ 5

ማንም ሰው ለስቃይ ወይም ለሌላ የጭከና ወይም አዋራጅ ለሆነ ድርጊት መዳረግ የለበትም።

(ከተባበሩት መንግሥታት የሰው ልጅ መብቶች መግለጫ የተወሰደና ለየት ባለ አገላለጥ የተጻፈ)

የሴት ብልት ጉንደላን የመቃወም ትግል ለሰው ልጅ መብቶች የሚደረገው ሥራና የሰው ልጅ መብቶቹም ሴቶችንም ልጆችንም በመጨመር ሁሉንም ሊያካትቱ እንዲችሉ የሚደረገው ሥራ አንዱ ዋና ክፍል ነው። በተጨማሪ፣ ትግሉ ባለቤቱ ራሱ በገዛ ሰውነቱ፣ በገዛ የግብረ ሥጋ ሁኔታው ለመወሰንና ከዚያ በተያያዘም ለኃይል ሥራ ላለመዳረግ ያሉትን መብቶች የሚመለከቱት የሕይወት ክፍሎች በሰው ልጅ መብቶች ውስጥ እንዲካተቱ የሚያደረግ ነው።

ወላጅነት በዕቅድ ኢንተርናሽናላዊ ፌዴሬሽን (IPPF) የተባለ ድርጅት በልዩ ልዩ መግለጫዎች ውስጥ የተጠቀሱት የሰው ልጅ መብቶችና ሌሎች መብቶች በግብረ ሥጋ ሁኔታና በመራባት ረገድ ምን ቦታ

እንደያዙ መርምሯል። በዚያ መነሻነትም የግብረ ሥጋ ሁኔታንና የመራባት መብቶችን የሚመለከት መግለጫ ተቀርጿል፤ በዚያም ውስጥ የሴት ብልት ጉንደላ በሁለት ነጥቦች ስር (2 እና 9) ተገልጧል። የሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞም ከተባበሩት መንግሥታት የልጅ መብቶች ስምምነት ድጋፍ የሚሆን ድንጋጌን ያገኛል (አንቀጽ 19) ። በዚያ አንቀጽ ቁልጭና ግልጥ ብሎ እንደ ተነገረው ልጅ «ከማንኛውም ዓይነት በአካሉ ወይም በአእምሮውና መንፈሱ ከሚደርስ የኃይል ሥራ፣ ጉዳት ወይም ግፍ ይጠበቃል»። በአንቀጽ 24.3 ደግሞ «ተዋዋዮቹ መንግሥታት፣ ለልጆች ጤንነት ጠንቅ የሆኑትን ባህላዊ ልምዶች ለማስወገድ የሚያስችለውን ዓይነተኛና ተገቢ ተግባር ሁሉ ይፈጽማሉ» ተብሏል።

የሴት ብልት ጉንደላ በ1980 መጀመሪያ ላይ በምዕራብ አገሮች እጅግም የታወቀ ጉዳይ ካለመሆን ተነስቶ በአሁኑ ጊዜ የፖሊቲካ ድጋፍን የያዘ ሥራ እየተካሄደለት ይገኛል። ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ስለ ሴቶችና ልጆች ጤንነት ባደረገው ጉባኤ የሴት ብልት ጉንደላ የሰው ልጅ መብቶችን የሚጥስና ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ድርጊት መሆኑና ልማዱን የሚቃወም ተግባር የመፈጸም ኃላፊነት ያለባቸውም ልማዱ የሚገኝባቸው አገሮች መንግሥቶች መሆናቸው በማያሻማ አኳኋን ተነግሯል። ትግሉም በዓለም ዙሪያ በብዙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጭምር በተጨባጭ ሁኔታ ይካሄዳል፤ በዚህም ረገድ ልማዱ በሚገኝባቸው አገሮች ያሉ የሴቶች ድርጅቶችና የማጣመሪያ (ኔት ወርክ) ድርጅቶች አስተዋጽኦ አነስተኛ አይደለም። የነኚህ ሴቶች ትግል ባይኖር ኖሮ የተባበሩት መንግሥታት በጉዳዩ ሊይዝ የበቃውን አቋም ምናልባት ላይዝ ይችል ነበር።

በመላው ዓለም በአሁኑ ጊዜ ከ100 እስከ 140 ሚሊዮን የሚሆኑ ልጃገረዶች ወይም ሴቶች የብልት ጉንደላ እንደ ደረሰባቸው ይገመታል። ከዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት WHO እንደ ተገኘው በየዓመቱ ተጨማሪ ሁለት ሚሊዮን ልጃገረዶች ጉንደላ ሊደርስባቸው ይችላል። የሴት ብልት ጉንደላን በመቃወም የሚደረገውንና ለሴቶችና ለልጆች የሰው ልጅ መብት፣ ለግብረ ሥጋ ሁኔታ መብትና ለርባታ መብት የሚደረገውን ትግል ለመቀጠል የሚያስፈልገው ምክንያት ሁሉ አለ።

ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው የሴት ብልት ጉንደላን የሚመለከቱትን ተጨባጭ ነገሮች ለማስታወቅ ነው። እነሱም የሴት ብልት ጉንደላ

ምን ማለት እንደ ሆነ የትስ እንደሚገኝ የመሳሰሉትን አርዕስት ይመለከታሉ። በተጨማሪም ጽሑፉ ስለሴት ብልት ጉንደላ አጀማመር የምናውቀውን ይገልጣል፣ በአሁኑ ጊዜ የሴት ብልት ጉንደላን በመቃወም የሚካሄደውን ትግልና ልማዱን የሚከለክሉ ሕጎችንም ያነሳል። ጽሑፉ የታቀደው ስለ ሴት ብልት ጉንደላ የበለጠ ለማወቅ ለምትፈልጉ ወይም ልማዱን በተግባር በመቃወም ለምትገኙ ሁሉ ነው።

## የሴት ብልት ጉንደላ ምን ማለት ነው?

የሴት ብልት ጉንደላና የሴት ግርዛት አንድ ነው። እሱም የል ጃገረዶችን የሴት ብልት የውጪ ክፍል ስል በሆነ መሣሪያ በሙሉ ወይም በከፊል መቁረጥ ማለት ነው። በዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት WHO አመዳደብ መሠረት የሴት ብልት ጉንደላ በአራት ዓይነት ይለያል።

### ዓይነት 1

የቂንጥር የላይ ሽፋን የሚቆረጥበትና አንዳንድ ጊዜም ቂንጥሩ ጭምር በሙሉ ወይም በከፊል የሚቆረጥበት።

### ዓይነት 2

ቂንጥር የሚቆረጥበትና የእምስ የውስጥ ከንፈሮች በሙሉ ወይም በከፊል የሚቆረጡበት።

### ዓይነት 3

የሴት ብልት የውጪው ክፍል ሁሉ ማለት ቂንጥርና የውስጡም የውጪውም የእምስ ከንፈሮች የሚቆረጡበት፤ ከዚያ በኋላ የእምሱን ስንጥቅ ለመድፈን የውጪው የእምስ ከንፈሮች አንድ ላይ የሚሰፉበት፤ ለሽንትና ለወር ደም መውጫ የሚሆን አንድ ትንሽ ቀዳዳ ዝቅ ብሎ ወደ ፊንጥጣው በኩል የሚተውበት። ይህ ዓይነቱ ኢንፊቡሌሽንም ወይም የፈርኦን ግርዛትም ይባላል።

### ዓይነት 4

ቂንጥርን ወይም ቂንጥርንና የእምስ ከንፈሮችን የመጠቅጠቅ ወይም የመሰንጠቅ። ድርጊቱ ቂንጥርንና የአካባቢውን አካል በማቃጠልም ሊፈጸም ይችላል። የአካሉን ክፍል መፈቅፈቅ

ወይም የስንጥቁን አፍ ዙሪያ መቅፈፍ ወይም ደም እንዲወርድ ወይም ቀዳዳውን ጠበብ ለማድረግ ሥጋን የሚፈረፍር ነገር ወይም ዕፅ እምስ ውስጥ የመጨርም ድርጊት ይገኛል።

ከነዚህ ዓይነቶች የተዋጡ ድብልቅ ዓይነቶችም ይገኛሉ። አዘውትሮ የሚገኘው 80 በመቶ ያህሉ (WHO ፋክት ሺት ቁ 241 ሰኔ 2000) የሴት ብልት ጉንደላ ቂንጥርንና የእምስ የውስጥ ከንፈሮችን በመቁረጥ የሚፈጸም ነው። ዓይነት 3 ኢንፊቡሌሽን፣ የጉንደላው ድርጊት 15 በመቶ ያህል ይሆናል። ስለ ልዩ ልዩ የሴት ብልት ጉንደላ ዓይነቶች በሚነገርበት ጊዜ «ሱና» ቀለል እንዳለ የጉንደላ ዓይነት አዘውትሮ ይጠቀሳል። «ሱና» ግን ከዓይነት 3 በቀር ሌሎቹን ዓይነቶች ሁሉ ሊጨምር ስለሚችል ወዲያውኑ የሚሰማ ስቃይንና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ስቃይን ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ በሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞ ውስጥ «ሱናንም» ልክ እንደ ኢንፊቡሌሽን በብርታት መታገል ያስፈልጋል።

## የጤንነት ጠንቆች

የሴት ብልት ጉንደላ የሚያስከትለው ውጤት እንደ ጉንደላው ዓይነትና መጠን ይለያያል። ከጉንደላው በኋላ ወዲያውኑ የሚከተለው ህመም፣ መድማትና መደንዘዝ ሲሆን አንዳንድ ልጃገረዶች ደግሞ የመንፈስ መቃወስም ሊደርስባቸው ይችላል። የሽንት መሄጃው ሊበላሽ ስለሚችል ብዙዎች የመሽናት ችግር ይገጥማቸዋል።

ችግር የሚደርስባቸው ሁሉም ባይሆኑም የልጃገረዶችን ጤና ለረጅም ጊዜ አዘውትሮ የሚያውከው የጉንደላ ውጤት፣ በተለይም ቁስሉ በሚድንበት ጊዜና በኋላም በዕድሜ በገፉበት የሕይወታቸው ዘመን የሚሰማቸው፣ የሆድ ህመምና ስቃይ ነው። ማሳከክ፣ ጠባሳ ማበጀት፣ ሲስት ማፍራት፣ ለለካፊ በሽታ መጋለጥ፣ መምከን፣ በመሽናት ጊዜ መቸገር የተለመዱ ሁኔታዎች ናቸው። በተቆረጡ የነርቭ ክሮች ም ክንያት በእምስ የውጪ ከንፈር ላይ የሚሰማ ህመም፣ በወር ደም ጊዜ የሚገጥም መቸገርም ከሴት ብልት ጉንደላ በኋላ ሊደርስ የሚችለው አንዳንዱ ሌላው ችግር ነው።

ልጃገረዶችን ገና በትንሽነታቸው ብልታቸውን እንዲጎነደሉ ማድረግ ይሻላል፣ ምክንያቱም በዕድሜ ከፍ ሲሉ ያሳለፉትን የጉንደላ ሁኔታ

አያስታውሱም የሚሉ ሰዎች አሉ። አዲስ የጥናት ምርምር ግን ሰውነትና የነርብ አዘገጃጀቱ ደርሶ የነበረውን ሁኔታ እንደሚያስታውሱና ሁኔታውም በትልቅነት ዕድሜ ጊዜ የሚገጥመውን ህመም ሊነካ እንደሚችል ይናገራል።

## የግብረ ሥጋ ሁኔታ

የሴት ብልት ጉንደላ አካላዊ ፍትወቷን የግድ የሚያስቀር አይደለም፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መርካትን ግን አስቸጋሪ ወይም የማይሆን ያደርግባታል። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የስሜት ቁንጮ ላይ ለመድረስ ስለሚቻልበት ሁኔታ የምናውቀው ትንሽ ነው፤ ቢሆንም የስሜት ቁንጮውን ሁኔታ ከሚነኩት ምክንያቶች አንዱ የጉንደላው ዓይነትና አፈጻጸሙ እንደ ሆነ ይታሰባል። ግርዛት በሴት የግብረ ሥጋ ሕይወት ላይ ምንም አዎንታዊ ዋጋ እንደሌለው በደንብ ይታወቃል።

ብልቷ ከተጎነደለ ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን መፈጸም ወንድንም የሚያሳምም ሊሆን ይችላል። በአንዳንድ ባህሎች ሴቷን ከሠርግ በኋላ የመክፈቱ ተግባር የባልየው ነው። በኢንፊቡሌሽን ዓይነት የተጎነደለች ሴት ቀደም ብላ የተከፈተች ቢሆንም ገፍቶ መግባቱ ወንዱን የሚያም ሊሆን ይችላል። ለግንኙነቱ ሲባል ሴቷን ለማሰቃየት ማስፈለጉም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

## ጋብቻ

የሴት ብልት ጉንደላ በአንዳንድ አገሮች ያለው ተፈላጊነት ድንግልነትን መፈተሽ በመባል በጋብቻ ውሎች ውስጥ ስምምነት ከሚደረግበት ክፍል ይታያል። ስምምነቱም የእጩው ሙሽራ ዘመዶች የጉንደላውን ጠባሳ አስቀድመው ለመመርመር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፣ ከዚያ በኋላ የሙሽራይቱ ዋጋ ይከፈላል። እንደ አንዳንድ የማኅበራዊ ሁኔታ ጠባይ መርማሪዎች አባባል በቀዳዳው ጠባብነት መጠን የሴቲቱ ደረጃ ከፍ ይላል፤ ይህም በጋብቻው ውል ድርድር ጊዜ ጠቃሚ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

ብልታቸውን ባልተገነደሉ ሴቶች ላይ የስም ማጥፋትና ከማኅበራዊ ሕይወት የማስገለል ድርጊት አዘውትሮ ይደርሳል። ስለዚህ በሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞ ውስጥ ወንዶችንም አለመተው አስፈላጊ ይሆናል፤ብልቷን ያልተገነደለች ለማግባት እሺ ሲሉ ብቻ ለውጥ ሊኖር ይችላል።

## ልማዱ በየትኞዎቹ አገሮች ይገኛል?

የልጃገረዶችን ብልት የመገንደሉ ባህል ከሁሉም በላይ የሚገኘው በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች ነው። በአንዳንድ የዓረብ ባሕር ክልል ውስጥ ባሉ አገሮች ማለትም በየመን፣ በኦማን፣ በተባበሩት የዓረብ ኤሚሬትና ባሕሬንም ውስጥ ይገኛል። እንዲሁም በኢንዶኔዢያ፣ በማሌዢያና በአንዳንድ በፓኪስታን፣ በሕንድና በፊሊፒንስ በሚገኙ የእስልምና ተከታይ ክፍሎችም ዘንድ ይገኛል። የሴት ብልት ጉንደላ የት እንደሚገኝ በትክክል ለመናገር አይቻልም፤ በአንድ አገር ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ እንዲሁም ከጎሳ ወደ ጎሳ የተለያየ ሊሆን ይችላል።

የሴት ብልት ጉንደላ ከሚገኝበት አገር ወደ ሌላ አገር የሚዛወሩ ሰዎች ከነባህላቸው ስለሚሄዱ የጉንደላው ባህል በምዕራቡም ዓለም ይገኛል። ስዊድን ውስጥ የሴት ብልት ጉንደላ ከሚገኝበት አገር የመጡ 16000 ያህል ሴቶች አሉ። በስዊድን አገር ክልል ውስጥ ልጃገረዶች በአሁኑ ጊዜ ብልታቸውን ይገነደሉ እንደ ሆነ አናውቅም፤ ነገር ግን ልጃገረዶቹ ወደ አገራቸው ወይም ወደ ሌላ አገር ተወስደ ው ካለ ሕግ እንዲገነደሉ የሚደረግ ይመስላል።

## ምንጬ

የብዙ ሺ ዓመቶቹ ባህል በወንድ በላይነት በሚካሄድ የማኅበረ ሰብ ዝግጅት ውስጥ ሴት ከወንድ በታች ከተደረገችበት ሥርዓት የመነጨ ይመስላል። አንድ ወንድ በሕይወቱ ዘመን ከሚያፈራቸው ፍሬዎች ሁሉ ሚስቱ ዋናዋ ስለነበረች በቁጥጥሩ ውስጥ መዋል የሚያስፈልጋት የሀብቱ ክፍል ሆነች። ሚስትን ረገጥ አድረጎ መያዝ የወንድን

የሥልጣን አቋም የሚያጠናክርና በሷ የግብረ ሥጋ ብልትና በምትወልዳቸው ልጆች ወዘተ ላይ መብት እንዲኖረው የሚያደርግ ነበር።

ካልተገረዙ የጸዱ የማይመስላቸው አንዳንድ ሴቶች አሉ፤ ሌሎች ደግሞ ያልተገረዙ ሴቶች ሽርሙጦች ይመስሏቸዋል። ብዙዎች ቂንጥርን እንደ ወንድ ትራፊ በማየት መቆረጥ እንዳለበት ያስባሉ። ከብልት ጉንደላ በኋላ ልጃገረዲቱ ሴት ትሆንና ተለቅ ያሉት በሚያካሄዱት ማኅበራዊነት ልትታቀፍ ትችላለች።

የሴት ብልት ጉንደላ በሚገኝባቸው በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ የሴት የግብረ ሥጋ ስሜት ቁንጮ የወንዱን የዘር ህዋሶች ስለሚገድል ፍሬ የማፍራቱ ሁኔታ ከብልት ጉንደላው በኋላ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለ። ትክክሉ ግን ግልብጡ ነው፤ የሴት ብልት ጉንደላ የማርገዝን ዕድል የሚቀንስ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

በመጨረሻም፣ ሴቶች ቂንጥራቸውን ካልተቆረጡ ከመጠን በላይ ቅንዝረኞች፣ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ግብረ ሥጋ ፈጻሚዎች፣ ወይም «ጎጂ» የሚሆን የራስን ፍትወት በገዛ እጅ የሚያረካ ድርጊትን በማጣመር ከመጠን ባለፈ ግብረ ሥጋዊነት ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አመለካከት እንደ ነበረ የታሪክ ዘገባዎች ያሳያሉ። በነዚህ ምክንያቶች ሴቶች በአውሮፓ እስከ 1900 ድረስ ይገረዙ ነበር።

## ባህል

ብዙ በዕድሜ ጠና ያሉ ሴቶችና በገዛ ጥረታቸው የሠለጠኑ አዋላጆች የሴት ብልት ጉንደላ ድርጊት ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ላይ አሁንም እየተፈጸመ እንዲገኝ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። እነሱ ከባህል ጋር በብርቱ የተያያዙ ናቸውና ነባር ልምዶች ተከታይነትን እንዲያገኙ ማድረግን እንደ ተግባራቸው ያዩታል። በአንዲት እናት ላይ ያለው ማኅበራዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ስለ ሆነ ግርዛትን ራሷ የማትፈልገው ቢሆንም የሴት ልጆቿን መገረዝ ለመምረጥ ትችላለች። ያልተገረዙ ልጃገረዶች በጋብቻ ገበያ ላይ ተፈላጊነት ስለሌላቸው እናቶች መገረዝን የልጆቻቸው የወደ ፊት ዕድል እንደሚከበርበት አንድ ሁኔታ ይመለከቱታል።

በሴት ብልት ጉንደላ ድርጊት ዙሪያ ያለውን ጠንካራ አስተሳሰብ መረዳት አስፈላጊ ነው። ከላይ እንደ ተገለጠው አንዳንዶች ቂንጥር የወንድ ትራፊ በመሆኑ ልጃገረዲቱ ሴት ለመሆን እንድትችል መቆረጥ አለበት የሚል እምነት አላቸው። ቂንጥር አድጎ አድጎ እንደ ወንድ ሙርጥ ትልቅ ሊሆን ይችላል የሚልም አስተሳሰብ አለ። በአንዳንድ ጎሳዎች ዘንድም ቂንጥር ልጅ በሚወለድበት ጊዜ ልጁን ሊጎዳና በ ቀጥታ ሊገድለው እንደሚችል ይታሰባል።

የሴት ልጆች ከእናቶቻቸው ጋር መመሳሰል ጥልቀት ያለው ሂደት ነው። አንዲት ትንሽ ልጃገረድ የሴትነት መለያ ለማግኘት እንድትችል እንደ እናቷ መሆን ያስፈልጋታል። የሴትነት መለያ በግርዛት ምክንያት ከደረሰው የብልቱ የውጭ ክፍሎች ለውጥ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ይመስላል፣ ስለዚህም ሴቶች ለውጡ የሴትነት አስፈላጊ ክፍል ሊሆን አይገባውም የሚል አስተያየት ለመያዝ እንደሚቸገሩ የጥናት ምርምር አሳይቷል።

## ሃይማኖት

ሃይማኖት በሴት ብልት ጉንደላ ድርጊት ረገድ ያለው አቋም አዘውትሮ ይተችበታል። ከክርስትና በፊትና ከእስልምና በፊት የነበረው ልምድ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ አልነበረም። የብልት ጉንደላ ድርጊት በምንም የሃይማኖት ጽሑፍ አልተጠቀሰም ወይም አልታዘዘም፤ ስለ ሴት ግርዛት በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቁራን ምንም አይገኝም። ቢሆንም የብልት ጉንደላ ክርስቲያኖችም ሙስሊሞችም ሌላ አምልኮ ያላቸውም ዘንድ ይገኛል።

በአንዳንድ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ክፍሎች ውስጥ የሴት ብልት ጉንደላ መደንገግ ነበረበት የሚል በስፋት ተቀባይነትን ያገኘ አስተያየት አለ። ነቢዩ መሐመድ የግርዛቱ ልማድ ነገር ባጋጠመው ጊዜ ልማዱን አልከለከለም፣ አፈጻጸሙ ከባድ ካልሆነ ፈቅዷል። ከዚህም የተነሳ ባህሉን መከተል የሚገባ መሆን ላለመሆኑ ክርክር አለ። በሌላ በኩል ደግሞ ነቢዩ መሐመድ የራሱን ሴት ልጆች ማስገረዙ አይታመንም፣ ግርዛትንም መቼውንም አላበረታታም።

የሴት ብልት ጉንደላ በክርስትና ሃይማኖት የታዘዘ አለመሆኑ በሙሉ ግልጥ ነው፣ ማንም ክርስቲያን ልጃገረድ በሃይማኖታዊ ምክንያቶች ልትገረዝ አትችልም። የተለያዩ የክርስትና ክፍሎች ቤተ ክርስቲያኖች ባህሉን የሚቃወም ያልቦዘነ ሥራ ያካሄዳሉ፤ ይኸውም ሆኖ ባህሉ የሚገኝበት ቦታ የሚኖሩ ክርስቲያን ልጃገረዶች ይገረዛሉ።

በአይሁድም ሕግ በኦሪት ወይም በሌሎች የአይሁድ ጽሑፎች የሴቶችን መገረዝ የሚያዝ ምንም ነገር የለም።

## ሕጎች

የሴት ብልት ጉንደላ በስዊድን ሕግ የተከለከለ ነው (1982:316)።

ሕጉ እንደሚከተለው ነው። —

1 §
የሴትነትን ብልት የውጪ ክፍል ለመቁረጥ ወይም ሌላ ኗሪ ለውጥ እንዲደርስበት ለማድረግ የታቀደ ድርጊት፣ ለድርጊቱ ፈቃደኛነት የተሰጠ ቢሆንም ባይሆንም፣ መፈጸም የለበትም (ሕግ 1998:407)።

2 §
አንቀጽ አንድን የሚጥስ አራት ዓመት ሊደርስ በሚችል እስራት ይቀጣል። ወንጀሉ ለሕይወት አስጊነትን ወይም ጽኑ ህመምን ካስከተለ ወይም በሌላ አኳኋን ከፍተኛ ግድ የለሽነትን ካመለከተ በከባድነት ይታያል። የከባድ ወንጀል ቅጣት አነስተኛው የሁለት ዓመት ከፍተኛው የአሥር ዓመት እስራት ነው። ሙከራ፣ ዝግጅትና ዱለታ እንዲሁም ወንጀልን አለማስታወቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ምዕራፍ 23 መሠረት ያስቀጣል (ሕግ 1998:407)።

3 §
የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ ምዕራፍ 2 ቁጥር 2 ወይም 3 ተፈጻሚነት ባይኖረውም ከላይ የተጠቀሰው ሕግ ወንጀል ያደረገውን ድርጊት የፈጸመ ሰው በስዊድን ፍርድ ቤት ይቀጣል።

በሕጉ መሠረት ማንኛውም ዓይነት የሴት ብልት ጉንደላ፣ ማለትም አብዛኛው የብልት ክፍል ከሚቆረጥበትና የእምስ ስንጥቅ ከሚሰፋበት

(ኢንፌቡሌሽን) ከከባዱ ዓይነት አንስቶ ቂንጥርን በስል ነገር እስከ መጠቅጠቅ ድረስ ያለው ሁሉ የተከለከለ ነው። ልጃገረዷቱ ወይም ሴቲቱ ድርጊቱን ብትፈቅድም የተከለከለ መሆኑን አያስቀረውም።

ስዊድን አገር የሚኖርና የብልት ጉንደላ በውጭ አገር እንዲፈጸም የሚረዳ ሰው፣ የተፈጸመው ድርጊት በተፈጸመበት አገር ሕጋዊ ቢሆንም እንኳ ሰውየው ስዊድን ውስጥ ሊቀጣ ይችላል። ይህ በሐምሌ 1 ቀን 1999 የወጣው ሕግ ቁጥር 3 ይዘት ነው። እንዲሁም ስዊድን ውስጥ እንደገና ኢንፌቡሌት ማድረግ፣ ማለት እምስን እንደገና አጋጥሞ፣ ለምሳሌ ከወለዳ በኋላ፣ መስፋት የተከለከለ ነው። እምስን በተቻለ መጠን እንደ ፍጥረቱ ለማድረግ ወደ ቀደሞ ሁኔታው መመለስ ያስፈልጋል። በማኅበራዊ አገልግሎት ሕግ ምዕራፍ 14 ቁጥር 1 መሠረት የተሠማሩበት ሥራ ልጅንና ወጣትን የሚመለከተው ሰዎች ሁሉ በሥራቸው አጋጣሚ የማኅበራዊ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አካለ መጠን ላላደረሱ ልጆች የጥበቃ ርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግበትን ሁኔታ ያወቁ እንደ ሆነ ይህንኑ ለመሥሪያ ቤቱ የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው። በዚህ ረገድ አንዲት ልጅ ልትገረዝ የምትችልበት ሁኔታ ላይ ትገኛለች ወይም ተገርዛለች የሚያሰኝ ነገር ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥምም የማኅበራዊው መሥሪያ ቤት ልጅቱን በጥበቃው ስር ለማድረግ ይችላል።

ስዊድን ስለልጆች ጤንነት፣ ደህንነትና መብት ጥበቃ በልዩ ልዩ መንገድ፣ በብሔራዊም በኢንተርናሽናላዊም ደረጃ ይሠራል። የሥራው አንዱ ክፍል የልጃገረዶችንና የሴቶችን ግርዛት የሚቃወም ተግባር ማካሄድ ነው። ስዊድንም እንደ ብዙ ሌሎች አገሮች አግባብ ያለው የኢንተርናሽናል ሕግ ተሳታፊ ነው፤ ሕጉም ስለ ልጅ መብቶች የተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት ነው። በአንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 3 ተዋዋዮቹ መንግሥታት ለልጆች ጤንነት ጠንቅ የሆኑትን ባህላዊ ልምዶች ለማስወገድ የሚያስችለውን ዓይነተኛና ተገቢ ተግባር ሁሉ ይፈጽማሉ በማለት ተደንግጓል። የሴት ብልት ጉንደላ የዚህ የተባለው ዓይነት ጠንቅ ነው።

## ስዊድን የሚገኙ የተገረዙ ሴቶች

የብልት ጉንደላ ከሚፈጸምባቸው አገሮች የመጡ 16000 ያህል ሴቶች (በ 2000) ስዊድን ይኖራሉ። ከነኚህ ውስጥ 14500 ገደማ

ያህሉ ከሱማሌ፣ ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ናቸው። ግርዛት ከሚፈጸምባቸው አገሮች የመጡ ከሰባት ዓመት በታች የሆኑ 2000 ያህል ልጆች ስዊድን ውስጥ ይገኛሉ።

ከአፍሪካ አገሮች ወደ ስዊድን ባለፉት ዓመቶች በመጡ ስደተኞች አማካይነት የሴት ብልት ጉንደላ በስዊድን የሴትና የመውለጃ ሀኪም ቤት ዘንድ የበለጠውን የአሁን ጊዜ ጉዳይ ሆነ።

## የብልት ጉንደላ ለደረሰባቸው ሴቶች ምን ርዳታ ይገኛል?

በዛሬው ጊዜ የብልት ጉንደላ የደረሰባቸውን ሴቶች መልሶ ለማደላደል የሚያስችሉ ብዙ ነገሮች አሉ። ከተመላላሽ ሀኪም ቤት የወጣቶችና የማሕጸን ክፍል እንዲሁም በሀኪም ቤት ከሚገኙ የሴት ክሊኒኮች ርዳታ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከወር ደም ጋር የተያያዘ ችግር፣ እብጠት፣ በባክቴሪያ መለከፍ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግር ወይም ከመጀመሪያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም እርግዝና ጋር የሚመጣ ችግር የተለመደ ርዳታ የሚጠየቅበት ችግር ነው። ስለ ችግሩና መድሃኒቱ ከሀኪም ጋር ንግግር ይደረጋል። የሚመረጠው የህክምና ርዳታም እንደ ግርዛቱ ዓይነትና የአፈጻጸሙ ሁኔታ ወዘተ ይሆናል። ውጤቱ ጥሩ ይሆናል፣ የቀድሞው ችግርም ይጠፋል።

ኢንፊቡሌሽን (ዓይነት 3) የተፈጸመባቸውን ሴቶች በተመለከተ አብዛኞቹ የሚከፈቱት ሀኪም ቤት በማደንዘዣ እንዲተኙ ከተደረገ በኋላ ነው፤ የሚቀደደውን ቦታ ብቻ በማደንዘዝም እንዲከፈቱ ይደረጋል። አንዳንድ ሀኪሞች በጨረር ኃይል መሣሪያ ይጠቀማሉ፣ ቁስሉንም የማዳን ጥሩ ውጤት ያገኙበታል። ቂንጥር በከፊል ተቆርጦ እንደ ሆነ በአካባቢው ያለው ለስላሳ አካል እንደ ልማድ እንዳለ ይተዋል፤ አለዚያ ከፍተኛ የቁስል ስሜት ሊያመጣ ስለሚችል ለምሳሌ ቁጭ ማለትና ሱሪ መልበስም ችግር ይሆናል። ከመክፈቱ የመቅደድ ሥራ ጋር በማያያዝ ሌሎች በጉንደላው ምክንያት የደረሱ ችግሮችም የሚቻል በሚሆንበት መጠን ይታከማሉ። አንዳንድ ሴቶች የመክፈቱ

ህክምና ከተደረገላቸው በኋላ ችግር ወይም ህመም ይደርስባቸዋል። ይህም ሊከላከሉ የሚችሉ የእምስ ከንፈሮች ባለመኖራቸው ምክንያት የሚመጣባቸው ለምሳሌ ተደጋጋሚ «የእንጉዳይ» እድገት ወይም ከመፋቅ የመጣ ቁስል ሊሆን ይችላል። ስለዚህም ቁስሉ በሚድንበት ጊዜ ሴቲቱ ወደ ህክምናው ቦታ እየተመላለሰች እንድትታይ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## የሴት ብልት ጉንደላን የመቃወም ሥራ

የሴት ብልት ጉንደላን የመቃወም ሥራ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ልዩ ልዩ መደቦችና ብዙ አገሮች ውስጥ ይካሄዳል። ባላነሰ ሁኔታም ባህሉ የሚፈጸምባቸው አገሮች ውስጥ የተቃውሞ አስተያየት እየጠነከረ ነው። «የሴቶችንና የልጆችን ጤንነት ስለሚነኩ ባህላዊ ድርጊቶች የኢንተር አፍሪካ ኮሚቴ (IAC)» የተባለው በ1984 በአፍሪካውያን ሴቶች ተቋቋመ። ድርጅቱም በተቋቋመባቸው ጉዳዮች ረገድ የተባበሩት መንግሥታት ምክር ሰጪ አካል ነው። የአፍሪካ አገሮች ብሔራዊ ኮሚቴዎች ስለ ብልት ጉንደላ ያላቸውን ተቃውሞ በፖሊቲካ መስመር፣ ለምሳሌ በገጠር ፕሮጀክት በማዘጋጀት፣ ያካሄዳሉ።

ድርጅቱ ጉዳዩን በዝምታ ተይዞ ከነበረበት ቦታ አውጥቶ በብዙ ባለዋጋ መድረኮች ዘንድ የተግባር ርዕስ እንዲሆን አብቅቶታል።

የሴት ብልት ጉንደላ ከሚፈጸምባቸው አገሮች የሚመጡትን ሴቶች በግብረ ሥጋዊነት አካባቢ ስላሉ ጥያቄዎች ማስተማር አስቸጋሪ ነው፤ ይኸውም ጥያቄዎቹ እንደ ነውር ስለሚታዩ ነው። ከዚያ ይልቅ ስለ ጤናና የሰውነት ክፍል መናገር በነውርነት ከሚታየው ነገር ለመላቀቅ የሚያስችል ዘዴ ይሆናል። ማሊ ውስጥ በሚካሄድ አንድ ፕሮጄክት ያልተገረዙ ሴቶች በየገጠሩ እየዞሩ ከተገረዙ ሴቶች ጋር ይነጋገራሉ። በዚያም ጊዜ የተገረዙት ሴቶች ብልታቸውን እንዲያሳዩና ያላቸውን ችግር እንዲናገሩ ይደረጋል። በተራቸውም የፕሮጄክቱ ሠራተኞች «ሙሉውን» ብልታቸውን በማሳየት ያልተገረዘውን ብልት ልዩ ልዩ ተግባሮች፣ ለምሳሌ በወር ደም ጊዜና በወለዳ ጊዜ ያሉትን፣ ይገልጣሉ። በዚህም ዘዴ በመገረዝና መገረዝ በሚያስከትላቸው ችግሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ማስተማር ይቻላል። በትምህርቱ የተገኘውም እውቀት ልማዱ ወደሚቀጥለው ትውልድ እንዳይተላለፍ ሊያደርገው ይችላል በሚያሰኝ ተስፋ ይታሰባል።

ሌላ በጋምቢያና በሲየራ ሊኦን የተዋጣለት ዘዴ ልማዱን በተግባር የሚፈጽሙትን ሰብስቦ «ሞያቸውን» የሚያካሄዱበትን ምክንያት መመርመር ነው። በቁጥር የሚበልጡቱ ሴቶች ለሆኑትና አብዛኛውንም ጊዜ የተማሩ ላልሆኑት ለነዚህ ሰዎች ሥራው ዋናው የገቢ ምንጫቸው ነው። እነሱም በማኅበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። በያዙት ሥራ ምትክ ያላቸውን ተሰሚነት የማይቀንስ ትምህርት፣ ለምሳሌ ለአዋላጅነት ሥራ ሊያበቃቸው የሚችል የሰውነት ክፍሎች ትምህርት፣ እንዲማሩ ሆነ። በተጨማሪም ደህና ብድርና ስለ አነስተኛ ንግድ ሥራ አካሄድ ትምህርት እንዲያገኙ ሆነ። ይህ ዘዴ በጣም የተዋጣለት ስለነበር ሌሎችም ገራዦች ያንኑ ትምህርት ለማግኘ ትእንዲችሉ በየቦታቸው የሚገኙትን ድርጅቶች ጠየቁ። ሲየራ ሊኦን ውስጥ ቀደም ሲል ከሴቶቹ 90 በመቶዎቹ ይገረዙ ነበር፣ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ከተደረገ በኋላ ግን ቁጥሩ ወደ 60 በመቶ ወረደ።

ውጤታማነታቸው የታየ ተጨማሪ ዘዴዎች፣ ከአንድ የዕድሜ መደብ ወደ ሌላ መደብ የመሸጋገሪያ ሥርዓት ውስጥ ለሚገቡ አዲስ ምልምሎች የሚሆኑ ሞዴሎችን በሥራ ላይ ማዋል ነው። በብዙ ቦታዎች ግርዛት አንዲት ልጃገረድ ወደ አደጉ ሴቶች ዓለም እንድትገባ የሚደ ረግበት ሥርዓት ነው። ከመገረዙ አሰቃቂ ሥርዓት ፋንታ ሌላ ሥርዓት እየተሠራበትና በመንደሮች ውስጥ፣ ለምሳሌ በኬኒያና በታንዛኒያ፣ ግርዛትን ቀስ በቀስ እየተካ ይገኛል። በጠቅላላው ይህ ተተኪ ሥርዓት የተገኘው የግርዛት መሠረት ከሆኑት ምክንያቶች ነው። እነሱም የአካል ንጹሕነት፣ ስለ ድንግልነት ያለ አስተሳሰብ፣ የቤተሰብ ክብር፣ የሴት ፍትወተኛነትን መቆጣጠር ናቸው። ከነዚህ ምክንያቶች በመነሳት ተተኪው ሥርዓት አብዛኛውን ጊዜ ከንጽሕናና የጤና ትምህርት ጋር እየተጣመረ ይዘጋጃል።

ሴኔጋል ውስጥ ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር ስለ ሰው ልጅ መብቶች የሚደረገውን ሥራ የሚካፈልና የሴት ብልት ጉንደላን በመቃወም የሚሠራ ቶስታን የሚባል አሜሪካዊ የግል ድርጅት አለ። የቶስታን መግለጫ ሰጪዎች የሰው ልጅ መብቶችን የሚመለከትና መንደረተኞች የተወሰኑ ችግሮቻቸውን እየለዩ ለመፍታት የሚበቁበትን ችሎታ የማሳደግ ዓላማ ያለውን የትምህርት ፕሮግራም (የመንደር የችሎታ ማስገኛ ፕሮግራም) እየያዙ በየመንደሩ ይሄዳሉ። ጥያቄዎቹም ከጤና ጥያቄ እስከ የመሪነት ትምህርትና የንግድ ሥራ እንዴት እንደሚካሄድ ጭምር ያሉ ጉዳዮችን ሁሉ ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። ባስገኘው ግልጥ ውጤት ሲታይ፣ የትምህርት ፕሮግራሙ የሴት ብልት ጉንደላውን የብዙ መንደሮች ኗሪዎች እንዲተዉት አድርጓል።

በተባበሩት መንግሥታት የልጆችና የሴቶች ጤና ዓለም አቀፍ ጉባኤ፣ ካይሮ (1994) እና ፔኪንግ (1995)፣ የሴት ብልት ጉንደላ ጉዳይ ታይቶ ነበር። በአጭሩ፣ ጥያቄው እንዲነሳና ልማዱ እንዲቀር ማድረግ የየአገሩ መንግሥት ኃላፊነት ነው ተባለ። የሴት ብልት ጉንደላ ሁልጊዜ ከሰው ልጅ መብቶች ጥያቄ ጋር መያያዝ አለበት። የአውሮፖ አንድነትም አባል መንግሥታቱ ባህሉን እንዲቃወሙ አሳስቧቸዋል። የሴት ብልት ጉንደላን በመቃወም ከሚሠሩ ሌሎች ማኅበሮች መካከል ፎርዋርድ፤ በሎንደን የሚገኘው የሴቶች ጤና፣ ምርምርና እድገት ፋውንዴሽን፤ ተመሳሳዩ በፈረንሳይ የሚገኘው ጋምስ፤ እንዲሁም መሥሪያ ቤትና ፕሮጄክት በብዙ አገሮች ያለው ኢንተርናሽናላዊ ድርጅት ሬይንቦ ይገኛሉ።

## የሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞ ሥራ በስዊድን

አንዳንድ ከውጭ አገር የመጡ ሰዎች ማኅበሮች፣ ለምሳሌ ስቶክሆልም የሚገኘው የሶማሌዎች ማኅበር፣ በመደበኛው ሥራቸው ውስጥ ወይም የጤና ጉዳይ ሥራቸው በማድረግ የሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞን ያካሂዳሉ።

የየተቦሪ ፕሮጄክት ዋና ዓላማ በጠቅላላው የሴቶችንና የልጆችን ጤና ለማሻሻልና በተለይ ደግሞ የሴት ብልት ጉንደላ እንዳይደርስ ለማድረግ ነበር። ፕሮጄክቱን ለማካሄድ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር አብሮ መሥራት ያስፈልግ ነበር። የሴት ብልት ጉንደላን በሚፈጽሙ የውጭ አገር ሰዎች ውስጥ ስለ ልማዱ የአስተያየት ለውጥ ሊደረግ የሚችለው ለባህል፣ ለአመለካከት፣ ለሃይማኖት፣ እንዲሁም ለአኗኗር ዓይነት ክብር በሚሰጥ የአሳብ ልውውጥ ብቻ ነው።

እንዲሁም ፕሮጄክቱ በተሠማሩበት ሞያ አጋጣሚ የተገረዙ ሴቶችንና መገረዝ ሊደርስባቸው የሚችሉ ልጆች ያሉባቸውን ቤተሰቦች ወደ ሚያገኙ ሰዎች ፊቱን አዙሮ ነበር።ፕሮጄክቱ «ስቃይ ሰጪው ባህል» በተባለው መግለጫ ውስጥ ተዘግቦ ይገኛል።

ሪስክ (RISK)፣ የሴት ብልት ጉንደላን የማስቀረት አገር አቀፍ ማኅበር፣ በስዊድን ውስጥ የብልት ጉንደላን ለመቃወም በ1994 ተመሠረተ። ማኅበሩ በአይኤሲ (IAC) ውስጥ ስዊድናዊው ተጠሪ ነው፤ በአውሮፓ አንድነት ውስጥ የጉንደላውን ባህል በመቃወም በሚሠራው በአውሮፓ ኔት ወርክም ይካፈላል። ሪስክ ከአፍሪካ ለመጡና በየአገራቸው ሰዎች

ዘንድ ጉንደላውን በመቃወም ለመሥራት ለፈለጉ ሰዎች የትምህርት ፕሮጀክት አካሄዷል። በተወሰኑ ቦታዎች የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ሴቶችን እንደ መግለጫ ሰጪዎች ቀጥረው በስቶክሆልም ከተማ ከውጭ አገር የመጡ ሰዎች በርከት ብለው በሚገኙባቸው ክፍሎች፣ በኡፕሳላ፣ በማልመና በሌሎችም ቦታዎች የተማሩትን እንዲያገለግሉ በት ያደርጋሉ። የማኅበሩ ሥራ የሚያተኩረው ከአፍሪካ የመጡትንና ሌሎች በባህሉ የተጠቃለሉትን በመርዳት ላይ ነው። ይኸውም አቋምንና አመለካከትን ለመለወጥና ልማዱ በአገራቸውም በሌላ የዓለም ክፍልም ሊቀር እንዲችል በሚደረገው ትግል እነሱ ራሳቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ነው።

በ RFSU አስተያየት የሴት ብልት ጉንደላ የቁጥጥር መግለጫና የሴትን ፍትወተኛነት መጨቆኛ ነው። በተጨማሪም RFSU የሴት ብልት ጉንደላ በሴት አካል ላይ እንደሚፈጸም ከባድ በደልና በዚያ ምክንያት መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችን እንደሚጥስ ድርጊት መታየት አለበት የሚል አስተያየት አለው።

የሴት ብልት ጉንደላ ተቃውሞ የሚካሄደው ይበልጡን በኢንተርናሽናል ደረጃ ነው። RFSU በየቦታው ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር በመሥራት ባህሉ ከሚገኝባቸው አገሮች ውስጥ እንዲጠፋ ለማድረግ ይፈልጋል። RFSU ስዊድን ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሠራው በመግለጫ በኩል ነው። በጽሑፎችና ስዊድን ከሚገኙ ከውጭ አገር ከመጡ ሰዎች ድ ርጅቶችና ሌሎችም ድርጅቶች ጋር በመሥራት ጉዳዩ እንዲታወቅ ለማድረግ ይቻላል። ከልዩ ልዩ ስዊድን ከሚገኙ ከውጭ አገር የመጡ ሰዎች ድርጅቶችና ማጣመሪያዎች (ኔት ወርኮች) ጋር ተባብሮ መሥራትም ተጨባጭ አሠራርን ያስከትላል።

ሬዳ ባርነን (ለልጆች መብት መከበር የቆመ ድርጅት) ጎጂ የሆኑ ባህሎች እንዲቀነሱ ለማድረግ በትጋት ይሠራል። የሥራውም መሠረት የተባበሩት መንግሥታት የልጅ መብቶች ስምምነት ነው። የሴት ብልት ጉንደላ የሰው ልጅ መብቶችንና የተባበሩት መንግሥታትን የልጅ መብቶች ስምምነት ይጥሳል፣ የሴት ግርዛትም የአካልንና የስነ ልቦናዊ-ማኅበራዊ ህክምናን የሚመለከቱ ከባድ ችግሮችን ያስከትላል የሚል አስተያየት አለው። ሬዳ ባርነን በልዩ ልዩ ባህሎች ውስጥ ይሠራል፣ ሰዎችንም የሚያየው በክብርና በተረጂነት መንፈስ ነው። በተጨባጭ በሚሠራ ሥራ ባህሉ ምን ነገርን እንደሚያሟላ ማወቅና በዚያ መሠረት ተጽእኖ ማድረግ ያስፈልጋል።

የሬዳ ባርነን የብልት ጉንደላ ተቃውሞ ሥራ በኢትዮጵያ፣ በኤር ትራ፣ በጊኒ ቢሳኦ፣ እና በምዕራብ አፍሪካ ክፍል በትጋት ይካሄዳል። ሥራው ከሁሉም በፊት በመግለጫና በአስተያየት ሁኔታ ሥራ አማካ ይነት በተወሰነ ቦታና በተወሰነ አካባቢ ይካሄዳል። ባህላዊ የአስተያየት ቀራጺዎች፣ ሕግ አውጪዎች፣ ውሳኔ ሰጪዎች፣ የሕግ ሰዎችና የሃይማ ኖቶች መሪዎች በቅድሚያ እንዲደረስባቸው የሚፈለጉ ክፍሎች ናቸ ው። ከወንዶች፣ ከሴቶች፣ ከልጃገረዶችና ከወንዶች ልጆች እንዲሁም የብልት ጉንደላን ድርጊት ከሚፈጽሙት ጋር በመሆን በገዛ ራሳቸው ኃላፊነት የሚሠሩ በቦታው የሚገኙ መግለጫ ሰጪዎችና ድርጅቶችም አስፈላጊ ናቸው። የሬዳ ባርነን ሥራ በሚቻለው መጠን ሁሉ በየተወ ሰነው ቦታ የሚገኘውን የአደረጃጀት ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባል።

ሲዳ ለብዙ አሥር ዓመቶች ከሁሉም በላይ በአፍሪካ የሚገኘውን የሴት ብልት ጉንደላን ተቃውሞ ሥራ በሚገባ ረድቷል። ይኸውም የተደረገው ከሁሉ በፊት እንደ አይኤሲ (IAC) ያሉትን ኤንጂኦ (NGO) ድርጅቶች (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) የመከላከያ ሥራና የአስተሳሰብ አቀራረጽ ሥራ ከሲዳ ጋር ተባብረው በሚሠሩ አገሮች የሁለት ወገን የሆነ ርዳታ አማካይነትና ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ WHO፣ UNFPA እና ዩኒሴፍ ባሉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች አማካይነት በተደረገ የብዙ ወገኖች በሆነ ርዳታ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሲዳ የጤና ክፍል፣ በሚያጠማምር (ኔት ወርክ) ድርጅት ላይ የተመሠረተውን የሬይንቦ ድርጅትን ይረዳል፤ ሬይንቦም በሥራው ውስጥ «የትንሽ ፕሮጄክት ርዳታ» የሚባል አለው፤ ያም በልዩ ልዩ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ትንንሽ ፕሮጄክቶችን በገንዘብ ሊረዳ የሚችልበት ነው።ሬይንቦ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የሴት ብልት ጉንደላን በመቃወም ሥራ ትጋት የሚያሳየውን አማኒታሬ የተባለውን የአፍሪካ ኔት ወርክን ያደራጃል።

የማኅበራዊ ጉዳይ መምሪያ በ1998 ከመንግሥት ስለ ሴት ብልት ጉንደላ የሦስት ዓመት ተግባር ተሰጠው። ተግባሩም «የብልት ጉንደላን አስቀድሞ ለመከላከል የሚረዳውን የአሠራር መንገድ የማስፋፋትና የማሰራጨት እንዲሁም ፕሮጄክት የመጠንሰስ ተግባር» ነው። (S98/5141/ST)። ተግባሩም ያተኮረው በአንድ በኩል አግባብ ባላቸው ሞያተኞች ላይ በአንድ በኩል ደግሞ አግባብ ባላቸው ከውጭ አገር በመጡ ሰዎች ላይ ነው። የማኅበራዊ ጉዳይ መምሪያ በተሰጠው የተግባር ክልል ውስጥ ዒላማ የተደረጉትን ክፍሎች የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ሥራዎችንና አሠራሮችን ፈጽሟል። ሥራውም አስቀድሞ በመከላከልና ወደ ቀድሞው የአካል ሁኔታ በመመለስ ረገድ ተካሄዷል፤ ያተኮረውም ችሎታን በማስፋፋት፣ አስተያየትን በማጎልመስና ሥራን

ቀጥሎ በመከታተል ላይ ነበር። ቀደም ሲል በ1996 ለተፈጸመው ለየተቦረ የሦስት ዓመት ፕሮጄክት ርዳታ ተደርጎ ነበር፤ እዚያ ያሉት የፕሮጄክቱ ኃላፊዎች ለመላው ስዊድን እንደ አማካሪ ለመሥራት ቀጠሉ። የስቶክሆልምና የማልመ ፕሮጄክቶች የገንዘብ ርዳታ አግኝተዋል፣ በርካታ የምርመራ መግለጫዎችም ከ1998 እስከ 2001 ባሉት ዓመቶች ወጥተዋል። ተጨማሪ በ www.sos.se ልታነቡ ትችላላችሁ።

## ምንጮችና ጽሑፎች


Agholme Johansson, Birgitta (1994), *Tusen om dagen...En fältstudie om kvinnlig könsstympning i Egypten.* (**የኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ፣ ቴኦሎጂ ኢንስቲቱሽን ዘንድ ይገኛል**)

Andersson-Brolin, Lillemor (1997), *Vi har ju alltid omskurit våra flickor! Om kvinnlig könsstympning.* Rädda Barnen. (**ከሬዳ ባርነን ማዘዝ ይቻላል**)

Carlbom, Aje m.fl. (2000). *Som Gud skapade oss – Förhållningssätt till kvinnlig omskärelse bland somalier i Malmö.* Malmö stads program Sexuell hälsa. ISBN 91-631-0051-7. Beställning: Malmö stads program Sexuell hälsa, Box 171 95, 200 10 Malmö. (**ከማልመ ከተማ የግብረ ሥጋ ጤንነት የተግባር ዕቅድ ማዘዝ ይቻላል። በስዊድንኛና በሶማልኛም በ**www.sos.se **ይገኛል።**)

Dorkeno, Efua (1994), *Cutting the Rose. Female Genital Mutilation: The practice and its prevention.* Minority Rights Publications. ISBN 1-873194-95-1. **ከ**Minority Rights Publications, 379 Brixton Road, London SW9 7DE, United Kingdom **ማዘዝ ይቻላል።**

Hosken, Fran P (1995), *Stop Female Genital Mutilation – Women speak. Facts and actions*. Women's International Network News. ISBN 0-942096-10-x. **ከ**WIN NEWS, 187 Grant Street, Lexington MA 02173 USA **ማዘዝ ይቻላል።**

Ismail, Nima & Sörman Nath Ylva (2000), *Ingen frågade mig. En rapport om kvinnlig könsstympning i Sverige.* Stiftelsen Kvinnoforum. **ከ** www.kvinnoforum.se **ወይም ከ**Kvinnoforum **በስልክ** 08-562 288 00 **ማዘዝ ይቻላል።**

Kulick, Don red. (1987), *Från kön till genus.* **የ**Aud Talle**ን** Ett sätt att skapa

kvinnor och män ጭምር የያዘ። Carlsson Förlag. ISBN 91-7798-124-3.

Omsäter, Margareta (1996), *Den smärtsamma traditionen – om Göteborgsprojektet mot kvinnlig könsstympning*. Göteborgs invandrarförvaltning. ISBN 91-630-4821-3.

Rahman, Anika & Toubia, Nahid (2000), *Female Genital Mutilation: A guide to laws and policies worldwide*. Zed, London. ISBN 1-85649-773-9.

*Socialstyrelsens meddelandeblad nr 5/00*, Ändringar i lagen (1982:316) med förbud mot könsstympning av kvinnor. በwww.sos.se/plus/skrift.htm ኢሜይል ማዘዝ ይቻላል።

*Kvinnlig könsstympning – ett utbildningsmaterial för skola, socialtjänst och hälso- och sjukvård*. Socialstyrelsen 2002. ISBN 91-720-660-4.

Sennemark, Said Musse & Abdulkadir (2002), *"Kvinnlig könsstympning. Om kvinnlig könsstympning som kulturarv. Tre somaliska workshops i Göteborg"*. ከ www.tidsspeglar.goteborg.se በ"Könstympning" ስር ይገኛል።

## ሌሎች ምንጮች

WHO በዌብ ቦታው ስለሴት ብልት ጉንደላ የአሁን ጊዜ ስታቲስቲክና መረጃ አለው። www.who.int/frh-whd/FGM/index.htmን ተመልከቱ።

### ልብ ወለዶች –

Devine, Laurie (1984), *Nilen*. Bokförlaget Forum. ISBN 91-37-10429-2.

Dirie, Waris (2001), *En blomma i Afrikas öken*. Bra Böcker pocket. ISBN 91-7133-812-8.

Kassindja, Fauziya & Miller Bashir, Layli (2000). *Vem hör mina tårar?* Bra Böcker. ISBN 91-7133-499-8.

Walker, Alice (1992), *Omskärelsen*. Trevi förlag AB. ISBN 91-7161-042-1.

መጽሔቱ (የዕቃ ቁ 2003-114-12)
Socialstyrelsen ከማኅበራዊ ጉዳይ መምሪያ የደንበኞች አገልግሎት
120 88 Stockholm ሊታዘዝ ይችላል።

ፋክስ 08-779 96 67፤ ኢሜይል socialstyrelsen@strd.se
የዌብ ሱቅ www.sos.se/plus/skrift.htm

መጽሔቱን ከማኅበራዊ ጉዳይ መምሪያ የዌብ ቦታም
www.sos.se ማውጣት ይቻላል።